ይቺ አለም!!!

ግጥም

ሃጂ አብደላህ ዩሱፍ

ጥንቅር

ኢምራን ኑረዲን

ይቺ አለም

ይቺ አለም የኔዋ እማማ

ልጆቿን በ እውቀት ገምግማ

ስታንቆጠቁጥ ሸልማ

አንድ ሰው ብቻ ረስታለች

ደፍሮ ሚነግራት አጥታለች!!

ሳይንቲስት፣ ደራሲ ፣ሽምጋይ

ውለታው ሁሉ ተወስቶ

በምድር ላይ ላበረከተው

ሲከበር NOBEL ተሰቶ

የኔ አለም የነቢ ታሪክ

ምን ሆና ተረሳት ከቶ???

(ሰለ ኋሁ አለይሂ ወ ሰለም)

//////////

የርሷ ነው ልጇን ታውቃለች

ቆይ ለምን ታርቀዋለች??

ስለ ነጻነት አስቦ

ወንድ ሴት ጎኑ ሰብስቦ

በትግል ቆስሎም ተርቦ

አለም ላይ ወንጀል ቀንሶ

ጨዋነት ባህሪን አላብሶ

ፈለጉን በሞት አውርሶ

እያየች ፈለጉ ሰፍቶ

የሰላም ትውልድ አፍርቶ

ምነው ሽልማት ማጣቷ

የሱን ስም አለማውሳቷ???



<<ፍትህ ሚዛንን ሃቅ አርጎ

ዘረኝነትን ጠራርጎ

ሰዎችን ለ መብት አፋልጎ

ፈለጉን ስላስቀመጠ

ለ ክብሩ ይሄ ተሰጠጠጠ...>>

ብላ ብትሸልም ምን አለ?

ሰው ሞቶስ ትሸልም የለ?

/////////

ከ ቁረይሽ መሃጸን ወቶ

ሃበሻ ያሳደገችው

ኸዲጃ በባህሪው ወዳው

ከ ንጉስ የመረጠችው

የልቧን የጇን አካፍላው

ካብራኳ ልጅ የሰጠችው

ማንበብም መጻፍም ሳይችል

ለአለማት የተመረጠው

የ አለማት ፈጣሪው አላህ

የ አለማት እውቀት የሰጠው

ጨለማን በብርሃን ሊገፍ

ብቻውን ትግል የቆረጠው

ለ ነብያት ትግል እና ገድል
ለ ታሪክ ተልኮ ዋቢ
ያለፈን፣ ያለን ፣መጪውን
በቁርዐን ተሰቶ አቅራቢ
አስጠንቅቅ አብስር ተብሎ
ለኛም ለመጪው ሲለፋ
ጉድጓድም ተቆፍሮለት
በስጋም መርዝ ቀርቦለት
ላዩ ላይ ፈርስ ሲደፋ
አለም ላይ ብርሃን ያኖረው
ለ አለም ሲል ሳይቆርጥ ተስፋ
የኔ አለም.....እንዴት ዝም አለች
ስለ ሙሃመድ ታማኙ???
ታሪኩን ሰልቦባት ይሆን
ሚዛኗ ወይም መዛኙ???
//////////

የጣልያን መሪ ሄርኩለስ

መልክተኞቹን ጠይቆ

ያልዋሸ ሃቀኛ ነብይ

ታላቅ ያላቸው አድንቆ

የሃበሻው ንጉስ ነጃሺም

የኖረው ትንቢት ጠብቆ

ተውራት ኢንጂልን ቁርዐንን

የመሰከረው ጠንቅቆ

ድሮም ሙስሊሞች ነበርን

አሁንም ያው ነን እያለ

እንባውን ካንጀቱ አውጥቶ

ፊቱ ላይ ዘርግፎት የለ

ይቺ አለም ልጇን ሸልማ ብታስተዋውቅ ምን አለ???

/////////

ምን አለ ይፋ ቢሸለም

ውለታው እንኳ ቢወሳ

ለማይቀር ይፋ መሆኑ ሲመጡ ነብዩ ኢሳ

አሳማም ኩፍር ሊታረድ
ነበር ተብሎ ሊረሳ
ያን ጊዜ በድፍን አለም
ይነግሳል የነብዩ ስም
ህዝብ ሁሉ እኩል ይሰልማል
ልዩነት አይተነፍስም
አላህ ነው ቀኑን የሚያውቀው
ይራቅም ወይም ይድረስም
ግን አሁን እስከዛው አሁን
እያለሁ ሳልሞት በቁሜ
ምናለ ብትሸልምልኝ
ነብዩን ይቺ የኔ አለሜ!!!
//////////
ምናለ ስለ ሃቅ አድራ
መዝና ገምግማ ስራ
<ላብራኬ ላፈር ለልጇ
በሂወት እንኳን ባይኖርም

ሽልማት ይድረሰው ከጇ
ለሰው ለእንሰሳ ለህዋው
ይድረስ አዋጇ >
ብትል ምን አለ ሽልማ???
ስርዐቱን የሽልማቱን
ሳር ዛፍም ባህር ቢሰማ???
/////////
ደስታ ነው ሃቀኛ ደስታ
የፍጡር ድንቅ ምስክር
ስለ ፈጣሪ ውለታ
ለሚጠፋ አለም ከማፈር
ለማይጠፋ አለም እርካታ
ደስታ ነው ሃቀኛ ደስታ!!!!
//////////
መካከለኛው ምሰራቅን
ችላ ካላሉት ባጋር ዘር
ይጠየቅ ቢባል ቢጀመር

ድፍን አፍሪካ ካለ አገር
ምስክር በዝቶ እስኪታክት
የ ብርሃን ሃቁ ሊናገር
በ አውሮፓ በስፔን ተሻግሮ
በቡኻሪ አገር ራሺያ
ፓኪስታን ህንድ አፍጋኒስታን
መልኩ ሳይጠፋ አልባኒያ
ዩጎዝላቭ ምድር ብትቃኝ
አዘርባጃንም ቦስኒያ
ቱርክን በሞላ ብትጠይቅ
በነቂስ በነ አልማኒያ
ከ ሩቅ ምስራቅም ላይጠፋ
ሲኦል ኮሪያ ቢጠየቅ
በ ቬተናም ቢከድ በ ቻይና
ፈለጉ ሊናገር ሊዘልቅ
ገራገር በሆነ ቋንቋ
ከ ቁርዐን ከሃዲስ ሊፈልቅ

ለአንድ አለም በአንድ አይነት ቋንቋ
የሰሩን የምንጨን ላይለቅ
በ እንግሊዝ ፈረንሳይ ብሎ
ወደ አሜሪካ ቢገባ
በርዞት ኋላ የቆጨው ቢጠየቅ ሃቫናም ኩባ
ጨዋ ስበእና ያዘለው ላይጠፋ
የፈለግ መልኩ
ይቺ አለም ዘንግታዋለች ባይገባት የልጇ ልኩ!!!
////////////////
መለከል መውትም አክብሮት የመጣው ቀኑን ቀይሮ
ፋጢማ ጠብቅ ስትለው እደጅ የቆመው ቆርቁሮ
ጂብሪልም አንገት የደፋው የሱን ሞት እንዳያይ ደፍሮ
አደራ ብሎን የሄደው ያለሙን የናቱን ኑሮ
መላክትም በሰልፍ የሸኙት ለዛኛው አለም ጅማሮ
እኔ እንጂ ትግስት ያጣሁት
ሳይሞትስ መች እሱ አዘነ
ፊርደውስም ከውሰርም አለው

ሽልማት ብርቁ መች ሆነ
እኔ እንጂ የያዘኝ ሲቃ
የተኛ ሁሉ እንዲነቃ
የ አለም ጨለማ ቢገፈፍ
መሃይምነት ቢያበቃ
የ ፍትህ ሚዛን ቢወጣ
ቢዘጋ የወንጀል ሳንቃ
አለም ከትግሉ እንድትማር
ቁጭት የያዘኝ እኔ እንጂ
ነብዩን መልሰሽ አምጪ
መች አልኳት ደግመሽ ውለጂ??
ግን ያልኳት ሽልሚልኝ ነው
ስራውን አይተሽ ፍረጂ
//////////
አጽናኙ መንፈስ ቅዱሱ
በትንቢቱ እለት ቢመጣ
ሴት በላ ከሆነ ትውልድ

ሴት ልጅን ነጻ ቢያወጣ
ለ አለም ዘሮች ነጻነት
የራሱን ጎሳ ቢቀጣ
አስር ሰው ለፍትህ ጥማት
መቶውን ገጥሞ ቢረታ
የ መለዐክት ወታደር ልኮ
ባገዘው የ አለማት ጌታ
የቆዳ ልዩነት ቁስሉ ከነ ቢላል ላይ ቢጠረግ
የሰው ዘር በፈጣሪ ፊት
አአአንድ ሶፍ ቢቆም በማእረግ
ሳያውቁት ዘሎ ስም ማጥፋት
ከታሪክ ሚዛን ማፈግፈግ
ምናል ቢያበቃ በ አለሜ
ለ ሰላም ለ ሰብዐዊነት
ነውና ፈለጉም ህልሜ።

ሃጂ አብደላህ ዩሱፍ